# የባህልና ስፖርት ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ/2015

አዲስ አበባ

## ማውጫ


| ቁጥር | ርእስ/ንኡስ ርእስ | ገፅ |
|---|---|---|
| ክፍል አንድ | መግቢያ | 3 |
| 1.1. | የጥቱ ዳራ (Backgraound of The Study) | 3 |
| 1.2. | የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ | 4 |
| 1.3. | የጥናቱ ዓላማ | 5 |
| 1.4. | የጥናቱ ወሰን | 5 |
| 1.5. | የጥናቱ አስፈላጊነት | 6 |
| 1.6. | መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች | 6 |
| ክፍል ሁለት | የሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ | 7 |
| ክፍል ሶስት | የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ | 8 |
| 3.1. | የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research Design) | 8 |
| 3.2. | የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling) | 8 |
| 3.3. | መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data Collection Methods) | 8 |
| 3.4. | የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ | 10 |
| ክፍል አራት | የሙስና ስጋት መረጃዎች ትንተና | 11 |
| 4.1. | የተቋማት አደረጃጀት | 11 |
| 4.2. | ተጠያቂነትን ማስፈን | 13 |
| 4.3. | የተቋማት ግልጽነት | 16 |
| 4.4. | አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ | 18 |
| 4.5. | የተቋማት ንብረት አስተዳደር | 19 |
| 4.6. | የግዥ አስተዳደር | 21 |
| 4.7. | የሰው ሃብት አስተዳደር | 23 |
| 4.8. | የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ | 25 |
| 4.9. | ፕሮጀክት አስተዳደር | 26 |
| 4.10. | ኦዲትና ቁጥጥር | 27 |
| 4.11. | የሙስና ስጋት ልየታ | 28 |
| ክፍል አምስት | መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ | 29 |
| 5.1. | መደምደሚያ | 29 |
| 5.2. | የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ | 30 |

# ክፍል አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው ወንጀል ሲሆን፤በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል ችግር ነው። ሌላው ሙስና በአደራ የተሠጠን ኃላፊነት ለግል ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ማስገኛ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም ነው። የሙስና መንሠራፋት የህግ የበላይነትን ያጣምማል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ያቀጭጫል፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያዳክማል፣ የኢንቨስትመንት ፍሰት ይገታል፤ እንዲሁም ሥርዓተ አልበኝነት እንዲንሰራፋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት አስፈላጊ ህጎች እንዲወጡ በማድረግ እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል። ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማካሄድ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው። በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡ ይሁን እንጂ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮች በዘርፍ ደረጃ ሲተገበሩ የሙስና ሥጋት ተጋላጭነታቸውን በየወቅቱ በመለየት የሚመጥን መፍትሔ የመስጠት ሥራ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ለማለት አያስደፍርም። ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል። እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲደራጁ በማድረግ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም።

በዘርፍ ስር ሊከሰቱ የሚችሉ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፤ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር እና የመረጃ አያያዝ ጥራት ችግር ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሠራሮች እንደሆኑ ይጠቀሳል። እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል።

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በባህልና ስፖርት ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግመገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 1.2. የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

የባህልና ስፖርት ዘርፍ በሚኒስቴር ደረጃ የሚመራ ሲሆን በስሩም ብሄራዊ ቤተመዛግብት፤ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፤ በብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር ተቋማት አሉ፡፡ ዘርፉን የሚመራው የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፤

- ባህልና ስፖርትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችን ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ- ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች እና ሀገር በቀል እውቀቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል፤
- የባህል ዘርፉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤መ) የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ የፈጠራ ችሎታዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የሀገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤
- በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ሥራዎችን ያከናውናል፤
- በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤
- የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ እንዲለሙ፣ ሥነ-ጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
- የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ እውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ሥራዎችን ያከናውናል፣ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

- የባህል፣ የስፖርትና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፤
- ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉም እና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤
- የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ሕክምና አገልግሎት ያደራጃል፣ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና እፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ የስፖርት ማህበራት ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ የሚውል ገቢ ማመንጨት እንዲችሉ ከዓላማቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሥራዎች እንዲያከናውኑ ይፈቅዳል፤
- የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ከውጪ የሚገቡበትንም ሁኔታ ያመቻቻል፤
- ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮች ሲዘጋጁና ሲካሄዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ብሔራዊ ስፖርት ልማት ፈንድ በሕግ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፤
- የስፖርት ፋሲሊቲዎች የሚተዳደሩበትን ስልት ይቀይሳል፤
- የአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከልን ጨምሮ ሌሎች የስፖርት ማዕከላት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ሥር በማደራጀት በአግባቡ መመራታቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

**አጠቃላይ ዓላማ፡-**

ዋናው የዚህ ጥናት ዓላማ በባህልና ስፖርት ዘርፍ የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ላይ ማካሄድ ነው፡፡

**ንዑስ አላማዎች፡-**

- የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣

- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ከህዳር/06/2015ዓም እስከ ሚያዚያ/30/2015ዓም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ በብሄራዊ ቤተመዛግብት፣ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ በብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር ተቋማት ላይ ተቋማዊ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር የግዥ አስተዳደር፣የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና ኦዲትና ቁጥጥር የአሰራር መርሆችን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ ምን እንኳን የምርጫ ቦርድ በዚሁ ዘርፍ ውስጥ ቢካተትም በተለያዩ ምክንያቶች ሚያስፈልጉ መረጃዎች ባለመገኘታቸው ከዚህ ጥናት ውጪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በአሰራር እና የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችና ብልሽቶች በመለየት የሙስና ቅደመ መከላከል እድል ስራዎች ለመተግበር የሚግዝ መሳሪያ ነው፡፡ ዋናው የግምገማዊ ጥናቱ አላማም የሙስና ስጋቶች በተጨባጭ መረጃ በተደገፈ በመለየት የመከላከል ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የአደጋ ለውጦችን ለመከታተል ለፀረ-ሙስና ትግል ሥራ እንደ መነሻ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህ መሻነት ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ የሚታዩ የሙሰና ስጋቶች በአስራ አንድ የትኩረት ጉዳዮች ለመየት የተካሔደ ነው፡፡ ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ፋይዳው በባህልና ስፖርት ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማት የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን በመለየት፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ በማመንጨት የሙስና መከላከል ስልት ማመላከት እና በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.6. መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

የጥናት ሥራው የተካሄደው ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሠራር ከመከላከል ረገድ ሊያከናዉኗቸው የሚገቡ ተብለው በተለዩ የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሲሆን በተጠየቁት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን የተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመጠየቅ መረጃ ሲበሰብ አንዳንድ ተቋማት ውስጥ የሚፈለጉና መረጃ የሚሰጡ የሥራ ኃላፊነት በቀጠሮ ምልልስ ማጋጠሙ፣ በተቋማት መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅቶ ባለመያዝ በተናጠል ለመሰበሰብ መቸገር፣ ሥራውን የሙስና ወንጀል ምርመራ አድርጎ በመውሰድ መረጃ ለመስጠት የማንገራገር ሁኔታዎች በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ተግደራቶች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ

የስፖርት ዘርፍ ብዙ ገንዘብና የሰው ሃበት የሚያንቀሳቅስ ነው፡፡ በይዘትም ሀገራዊ አህጉራዊ እና ዓለምአቀፋዊ መገለጫዎች አሉት፡፡ ይህም ለሙስና ተጋለጭ ያደርገዋል፡፡ በስፖርት ዙርያ የሚታዩ ሙስናዎች ሁለት መልክ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የመጀመሪያው መልክ የሚገለፀው ተሳታፊዎች በሚደርጉት መሰተጋብር ነው፡፡  አትሌቶች፣ የስፖርት ኃላፊዎች እና ዳኞች ውጤት ለማስቀየር የመደረግ በጉቦ ወይም ውለታ በመቀባበል የሚሳተፉበት ነው፡፡ ሁለተኛው መልክ ስፖርተዊ ሙስና የውድድር ምድቦች፤ ውድድሮች ማሰተናገድ እና ስፖርት ሃላፊዎች ምርጫ የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ አገሮች ለመመረጥ ወይም ዜጎቻቸው ለማስመረጥ በሚያደርጉት ጥረት ድምፅ ለመግዛት ሙስናን ጥቅም ላይ ያውሉታል (Hwang, 2016)፡፡ በተጨማሪም United Nations Office on Drugs and Crime (2021) ባደረገው ጥናት የሚከተሉትን በሰፖርት ዙሪያ የሚከሰቱ መስናዎችን የተደራጁ ወንጀለኞች የሚሳተፉበት፤ አወራራጅ ድርጅቶች የሚሳተፉበት፤ የስፖርት ውድድሮች ማጨበርበር፤ ውድድር ማዘጋጀት፤ የመገናኛ ብዙሃን ስርጭት እና ስፖርት አመራር የሚገናኙ በማለት አስፍሯል፡ ፡ ይህ ጥናት የዘርፉ ውስብስበነት በመጥቀስ አስፈላጊ የመከላከል ስራ መተግበር በወሳኝ መልኩ አመላክቷል፡፡

ሌላኛው ሙስና ከሚሰተዋልባቸው የባህል ዘርፎች ወስጥ ሚዲያና የመዝናኛው ኢንዳስትሪ ነው፡፡ **የመገናኛ ብዙሃን እና የመዝናኛ  በባህሪው በጣም ከፍተኛ የገበያ ውድድር የሚስተዋልበት መሆኑ ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡** በተለይ የፊልም ኢንዳስትሪ ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ ዋናው ነው፡፡ **የተፋጠነ የፊልም ቀረፃ ለማካሄድ፣ ምቹ የቀረፃ ቦታ ለማግኘት፣ የአገር ውስጥ ፊልም ሠራተኞች ጋር መልካም ግኑኝነት ለመፍጠር እና አስፈላጊ የቀረፃ እቃዎች ለማጓጓዝ ክፍየዎች የመፈፀም ተግባር ውስጥ ይገባሉ፡፡  በተለይ ከአገር ውጭ የሚደረጉ ቀረፃዎች ይህ ዓይነት ሙስና ይስተዋልባቸዋል** (Siegel, 2016)**፡፡** ሙስና በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ህይወት ላይ በተጨማሪ ህገወጥ የቅርስ ዝውውር ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው፡፡በቅርሶች እና ቅርሶች ላይ የሚደረገው ህገወጥ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጨመር አዝማሚያ እያሳየም ነው፡፡ ይህም ታሪካዊ ትውስታን ብቻ ሳይሆን የህዝቡን ማንነትም መንካቱ አይቀርም፡፡ የቴክኖሎጂ ግስጋሴው በሕገ-ወጥ መንገድ ቅርሶችን እና ቁሳቁሶችን ከአንድ አገር ወደ ሌላኛው በቀላሉ ለማውጣት እና ለማጓጓዝ አስቻይ ሁኔታ እየፈጠረ በመሆኑ ስቆቱን

በማባባስ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በቅርስ ስርቆት መንገድ የሚፈፀሙ ሙስናዎች መከላከል ካልተቻለ አገሮች ከታሪካዎች እና ከቅርሳቅርሳቸው የሚየገኙትን ጥቅም ከማስቀረት በተጨማሪ በማንነታቸው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል (Dalena, 2016)፡፡

# ክፍል ሶስት

# የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና ትንተና ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር የባህልና ስፖርት ዘርፍ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ በአብዛኛው ዓይነታዊ እና በተወሰነ ደረጃ የአሃዛዊ (mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በማጣመር በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆነው መረጃም ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የመሰብብ ስራ ተሰርቷል፡፡

## 3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)

ይህ ጥናት በዋነኝነት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና በስሩ ባሉ ተጠሪ ተቋማት ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የአይሲቲ የጥናት መረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

## 3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

### 3.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ

በዚህ በዘርፍ ሥር በተደራጁት ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 11 የትኩረት ርእሰ ጉዳዮችን የመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመረጃ መሰብሰቢ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጠይቅ ዙርያ ላይ ለመረጃ ሰበሳቢዎች ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ በመፍጠር መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብኣት የሚሆነው መረጃ የተሰበሰበባቸው የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮችም ዝርዝር በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ቀርቧል፡፡

### 3.3.2. የሙስና ሥጋት መንስኤዎችንና አመላካቾችን ልየታ

የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ሊያሳዩ የሚችሉ አመላካች ርዕሰ ጉዳዮች መለየት ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነትም አስራ አንድ ተለየይተው የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቁ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት የትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመከናወኑ ወይም ሲከናወን የተስተዋሉ ችግሮችን ከሙስና እና ብልሹ አሠራር አንፃር በመቃኘት የሙስና የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካች መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያው መጠይቅ ውስጥ የተካተቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሰ ጎዳዮች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ተቋማዊ አደረጃጀት፡-** ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አስራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተልዕኳቸውን የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የህግ ጥሰቶችን በህግ ስርዓት በማስተካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ግልፅነት፡-** የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙበት ዋና አላማ ለህዝብ አገልግሎት መስጠት እስከሆነ ድረስ ተግባር፣ሃላፊነታቸውና የአሰራር ስርዓታቸውን ለተገልግጋዩ ማህበረሰብ ግልፅና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት አገልሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተደራሽነት መርሆች ምን እደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ፡-** ሙስና እና ብልሹ አሰረሰርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣አፈፃፀምንን ለማሻሻል ተቋማት የአሰራር መመሪያ፣ አዋጅና ደንብ ያወጣሉእንዲሁም በየ ጊዜው ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት ቁመና ምን እንደምሚስልና የሚያወጧቸው የአሰራር መመሪያዎች ምን ያክል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስለመናቸው የምንፈትሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር፡-** የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ አገልግሎት የማይሰጡ፣ መወገድና መጠበቅ ያለባቸው የተቋማት ንብረቶች የተያዙበት ስርዓት ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

- **ተቋማዊ የግዥ አስተዳደር፡** ግዥ በእቅድ፣በመመሪያና በቴክኖሎጅ በታገዘ መልኩ በመፈፀም ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉበትን ስረዓትና አሰራር የመፈተሸበት የጥኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሰው ሃብት አስተዳደር፡** አቅምና ብቃት ያለው የሰውሃበት መረጃ አያያዝን እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የሚያስተዳድሩብትን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሀብት ምዝገባ፡ ሀብት** ምዝገባ አንዱ የግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርህ ስለሆነ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብታቸውን ስለማስመዝገባቸው የምንፈሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ፕሮጀክት አስተዳደር፡** ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ፕሮጀክቶች የሚያስተዳድሩበትና የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ብክነትን በቀነሰ እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመሆኑ የምንገመገምበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የኦዲት ቁጥጥር፡** የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚገመገሙበት፣ ውይይት የሚደረግበት እንዲሁም የማስተካያ አስራሩ ምን እንደሚመስል ተቋማት የሚገመገምበት የትኩረት መስክ ነው
- **የተቋማትን ልዩ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ልየታ፡** ተቋማት የጋራ ከሚያደርጓቸው የድጋፍ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የተቋቋሙት ልዩ ተልዕኮ ያላቸውን የተጋላጭነት ሁኔታ የተለየ የሚያደርገው በመሆኑ ልዩ የሆኑት የሚታዩበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

## 3.4. የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ

የተሰበሰበው መረጃ ከመተንተቱ በፊት ከየተቋማቱ መረጃዎች በርእሰ ጉዳች ከተለዩ በኋላ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተደራጀው የሰነድ መረጃ ለማውጣት (extract) እንዲቻል በየዘርፉ የጥናት ቡድኖች ተዘጋጅተው ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ መረጃው በማውታት ሂደትም በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ ተቋማቱ ማከናወን ሲገባቸው ያለከናወኑት ተግባር፣ ተግባራቱን ሲያከናወኑ የተስተዋሉ ችግሮችንና ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም በተግባራት ክንውን ወቅት የተስተዋሉ ለሙሰና የተጋለጡና ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አስችሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ከአሉት ዓይነታዊ መረጃ አተናተኖች ውስጥ ጭብጥ ተኮር (Thematic Analysis) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ሪፖርት አቀራረብም አይነታዊ ገለፃ ዘዴ (Descriptive

Method) ተግባራዊ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትንተናው ሂደትም መረጃዎች በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳረቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ይህም ድምዳሜ ላይ ከመድረሳችን በፊት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

# ክፍል አራት

# ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ትንተና

በባህልና ስፖርት ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ትንተና በአስራ አንድ ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፦

## 4.1. የተቋማት አደረጃጀት

በባህልና ስፖርት ዘርፍ ተጠሪ ከሆኑት ተቋማት በተፈቀደው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት መሰረት በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፤ በብሄራዊ ቤተመዛግብት፤ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፤ በብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር የስነምግባር መከታተያ ክፍል ተደራጅተዋል። የስነምግባር መከታተያ ክፍል በሰው ሀይል ከማሟላት አንጻር የባህልና ስፖርት ሚ/ር መ/ቤት የተፈቀደለትን አራት የስራ መደብ ተሟልቷል። የብሄራዊ ቴያትር፣ ስፖርት አካዳሚ፣ ብሄራዊ ቤተመዛግብት ከተፈቀደላቸው ሶስት የስራ መደብ ውስጥ ሁለቱን በሰው ኃይል ያሟሉ ሲሆን፤ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ግን ከተፈቀደለት ሦስት የስራ መደብ ውስጥ አንዱን ብቻ የመደበ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል።

የስነምግባር መከታተያ ክፍል ቢሮን በተመለከተ አራቱ ተቋማት ቢሮ ያላቸው እና ስራቸውን ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲሰሩ የሚያስችላቸው መሆኑ እና በበለጠ ትጋት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ያግዛቸዋል ተብሎ ይታሰባል። ሌላው የብሄራዊ ቤተመዛግብት ግን የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ከሌላ የስራ ክፍል ሠራተኞች ጋር በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ የተዳበለ መሆኑን እና ለስራቸው ምቹ ሁኔታ አለመኖሩን በአካል በመገኘት በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከብሄራዊ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በስተቀር በአራቱ ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍል ለቢሮአቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች የተሟሉላቸው መሆኑንም ለመመልከት ተችሏል።

ዕቅድን በተመለከተ ከብሄራዊ ፀረ-አበረታች ኤጀንሲ በስተቀር በአራቱ ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች የ2015 ዓ.ም ስራቸውን ለመስራት በተቋማቸው የጸደቀ እቅድ ያላቸው መሆኑን ከተሰበሰበ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም በዘርፉ ከሚገኙ ተቋመት ውስጥ

አራቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሞላ ጎደል ይህን ተልዕኮ ለመወጣት በብቁ ቁመና ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ቀሪው አንድ ተቋም ግን በጅማሮ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት ያለው ቁመና ብቁ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስነምግባር ክፍሎቹ ውጤት ሊያመጣ በሚችል አግባብ መደራጀታቸው አስፈላጊው የሰው ሀይል፤ የቁሳቁስ እና በቂ በጀት ቢሟላላቸው በየተቋማቱ ውጤታማነት ላይ የራሳቸውን ጉልህ ድርሻ ያበረክታሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ በአራቱ ተቋማት የተስተዋለው በቂ የሰው ሀይል አለማሟላት፤ ክፍሎቹን በበቂ በጀት አለመደገፍ እና ለስራ ምቹ ሁኔታዎች አለመፍጠር እንዲሁም የአንዱ ተቋም በጅምር ላይ መሆን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከለላከል የሚደረገውን ጥረት በብርቱ ይጎዳል፡፡

በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ በአምስቱም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተጨማሪ የሀብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ከላይ ከተገለጹት አደረጃጀቶች በተጨማሪ የተጠናከሩ ባይሆኑም በአምስቱም ተቋማት ውስጥ የህግ እና የተቋማዊ ለውጥ ክፍሎች ተደራጅተው የሚገኙ መሆናቸውን በየተቋማቱ ከቀረቡ መረጃዎች ለማጣራት ተችሏል፡፡ እነዚህ አደረጃጀቶች አለመጠናከራቸው ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ በተቋም ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አራቱ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ዘዴ በአካል በመገኘት ጥቆማ የሚሰጥበት፣ የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተገበሩ ሲሆን፤ አንዱ ተቋም (የብሄራዊ ፀረ-አበረታች ኤጀንሲ) ግን የጥቆማ መቀበያ ስርዓት አለመዘርጋቱን በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

በተቋማት የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የጥቆማ ስርዓት አይነተኛ የትግል መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ ተቋማት ይህን ስርዓት መዘርጋታቸው የሚበረታታ ቢሆንም ስርዓቱ ባልተዘረጋበት አንድ ተቋም የሙስና ስጋትን ለመለየትና የእርምት እርምጃ ለመውሰድ አሉታዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዘርፉ የሚገኙ የሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ

ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም። ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም የጋራ ትንተና ለማካሄድ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ አለመወጣታቸውን የሚያመላክት ነው።

የየተቋማቱ የሕግ ክፍሎች ራሳቸውን ችለው ቢደራጁም በሁሉም በሚባል ደረጃ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥባቸው አሠራር ስለመኖሩ መረጃ አላቀረበም። እንዲሁም በተቋማቱ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት መኖሩን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። በመሆኑም በአብዛኛዎቹ በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት አለመሰጠቱ የመንግስትን ጥቅም ሊጎዳ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል።

ከዚህ በመነሳት ሊከሰቱ በሚችሉ የሙስና ስጋቶች

- የስነ ምግባር ክፍሎች በአግባቡ የተደራጁ አለመሆናቸውን የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ። ሁሉም ሊባል ቢሚል ደረጃ በሰው ሃብት አለመሟላታቸው አደረጃጀቱ ላይ ያለው ውስንነት ማሳያ ነው። ይህም ስነምግባር ክፍሎች በአዋጅ የተጣለባቸወን ሃላፊነት ለመወጣት ያላቸው እድል ሊያጠበው ይችላል። በተጨማሪ የስራ ክፍሎቹ የበጅት ነፃነት ያላቸው አይመስሉም። ስራ ለመስራት ሲስቡ በአመራሩ በኩል ካለፀደቅ ተግባራዊ ስራ መስራት አይችሉምና። በጀት በፑል መሆኑ በውስን መልኩ የስነምግባር ክፍሎቹ ለጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ሊያደርጋቸው እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው። በተቋማት የአደረጃጀት ውሰንንት መኖሩ አመራሩ ሙስናን ለመዋጋት ያለው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን የሚያመላክት ሊሆን ይችላል።
- በጥናቱ ሂደት ከታዩት የአደረጃጀት ውስንነቶች ውስጥ የህግ ክፍሎች የሚጫወቱት ሚና ክፍተት ያለበት መሆኑን ነው። የህግ ክፍሎች ውሎች እና ስምምነቶች ላይ አስተያየት የሚሰጡበት ልምድ የዳበረ አመሆኑን ከህግ ጥሰት የሚመነጩ የጥቅም ግጭቶች ለመከላከል ያለው እድል ሊያጠበው ይችላል። በተጨማሪም ስልጣንን አለአገባብ መገልገል ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል የሚጠበቅ ነው። ተጨማሪም የጥቆማ ስርኣት በተጠናከረ መልኩ ተግባረዊ አለመደረጉ ተጠያቂነት ከማስፈን አንፃር ክፍተት ሊፈጠር እንደሚችልም መገንዘብ ተገቢ ነው።

## 4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

ተጠያቂነት አንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት ጋር በተያያዘ አፈፃፀሙን በመገምገም ለሚፈጠሩ ጉድለቶችና ጥፋቶች ኃላፊነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በተለይ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ መንግስታዊ ተቋማት የሚያስተዳድሩትን የህዝብ ሀብት በተገቢው መንገድ ለህዝብ አገልግሎት የማዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩም አስፋላጊውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ የህዝብ ሀብት እንዳይባክንና የመንግስት ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የተሰጣቸውን ስልጣን አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳያውሉ የማረጋገጥ ስራ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር ተያያዥ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

በባህልና ስፖርት ዘርፍ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አምስቱ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራርን በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ስለማካሄዳቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም የሚያሳየው በዘርፉ ያሉ ተቋማትን ለሙስና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት ግልጽነትና ተጠያቂነት ከመፍጠር አኳያ የተጠናከረ ስራ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ነው፡፡ በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የደንበኛ እርካታ በገለልተኛ አካል ስለማስጠናታቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ ይሁን እንጂ ብሄራዊ ቤተመዛግብት የደንበኞች እርካታ በተቋሙ የለውጥ አመራር ዳይሬክቶሬት ያስጠና መሆኑን ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር የብሄራዊ ቤተመዛግብት እና ባህልና ስፖርት የስነምግባር ደንብ ያዘጋጁ ሲሆን፣ የቀሩት ሶስቱ ቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) ስለማዘጋጀታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በባህልና ስፖርት ዘርፍ ስር ከሚገኙ አምስት ተቋማት ውስጥ አራቱ የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈጸማቸው በፊት ጥቆማዎች ደርሰው ቅድመ መከላከል ስራዎችን ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ነገር ግን የባህልና ስፖርት ሚ/ር በአበል አከፋፈል እና አላግባብ የሚወጡ ወጪዎችን መቀነስ ጋር በተያያዘ ጥቆማ ደርሶ ቀድሞ የመከላከል ስራ የተሰራ መሆኑን ከመረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት በ13 ፈጻሚዎች ላይ ባቀረቡት ክሶች ዘጠኙን (69 በመቶ) ተቋማቱ ረተዋል፡፡ ቀሪዎቹ አራት ክሶች በሂደት ላይ የሚገኙ

መሆናቸውን ከመረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተቋሙ ባለፉት ሁለት አመታት የቀረቡ ቅሬታዎች መኖራቸውን በተመለከተ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ አምስት ቅሬታዎች ቀርበው ለአምስቱም ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ባህልና ስፖርት ሚ/ር አራት ቅሬታዎች ቀርበው ለሶስቱ ምላሽ የሰጠ ሲሆን፤ አንዱ በሂደት የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የቀሩት ሶስት ተቋማት ምንም ቅሬታ ያልቀረበላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለፀረ-ሙስና ትግል የአመራር ሚና ወሳኝ መሆኑን የተለያዩ የጥናት ውጤቶች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን በባህልና ስፖርት ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን ሪፖርት በተቋማቱ የበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግባቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን ሪፖርት በበላይ ሃላፊዎች ግምገማ አለመደረጉ፣ በዘርፉ ስር በሚገኙ አንዳንድ ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት አለማድረጋቸው፣ የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል አለማስጠናት፣ በተወሰኑ ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) አለመኖር እና ጥቆማን መሰረት አድርጎ የቅድመ መከላከል ስራ ያለመስራት ተቋማት በደንበኞች ሊነሱ የሚችሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት አስቸጋሪ ከማድረጉ በላይ የተጠያቂነት ስርአት ለመዘርጋት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት ሊከሰቱ በሚችሉ የሙስና ስጋቶች

- በዘርፉ ባሉ ተቋማት ላይ የተደረገ ጥናት በመረጃ ስብሰባው ሂደት የተጠቀሰ ቢሆንም በጥናት ላይ ተመስርቶ ተጠያቂነት የሚያሰፍን እርምጃ ስለመወሰዱ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም የአፈፃፀም ግምገማዎች የሚካሄዱ መሆናቸው ቢመላከተም ግምገማውን መሰረት በማደረግ የሚወሰዱ እርምጃዎች ስለመኖራቸው በሰነድ ፍተሻ ወቅት ማየት አልተቻለም፡፡ ከዚህ ተነስተን መገንዘብ የሚቻለው በዘርፉ ያለው አመራር ተጠያቂነት በማስፈን በኩል ቀጣይነት ባለው መልኩ እንቅስቃሴ የማድረግ ውስንነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ለአብነት በስፖርት ጉዳዮች የሚታዩ ሙሰናና ብልሹ አሰራሮች ለመከላከል ከሚበረክተው አስተዋፀኦ አኳያ ዘርፉ ተጠቂነት ባለው መንገድ መምራት ካለተቻለ ጉዳቱ የከፋ ሊደርገው ይችላል፡፡ የመዝናኛው ኢንዳስትሪ የሚያንቀሳቅሰው ሃብት እና ከሚሳተፍበት ሰው ብዛት ተጠያቂነት ባለው መልኩ

ለመመራት የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት ካልተቻለ ሙሰናን መዋጋት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

- በዘርፉ ተቋመት የደንበኞች እርካታ በገለልተኛ አካል ለማስጠናት ያካሄዱት እንቅስቃሴ አለመኖሩ ተጋልጋዮች የሚያጋጥማቸው ችግሮች ለመፍታት የሚስችለውን እድል ሊያመክነው ይችላል፡፡ በተለይ የሚካሄዱ ጥናቶች የሙስናውን ስፋት እና ጥልቀት ማሳየት ካልቻሉ ተጠያቂነት የማስፈኑ ስራ ጥቄ ምልክት ውስጥ ሊከተው እንደሚችል መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚከሰቱ ሙስናዎች እና ብልሹ አሰራሮች ከተገልጋዮ የበለጠ መረጃ ሊሰጥ ሚችል አካል ባለመኖሩ የተገልጋዮች ጥናት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች ለመለየት ተገልጋዩ ማሳተፍ ፋይዳው ብዙ ነው፡፡
- ይህ በእንዲህ እንዳለ በዘርፉ የተከሰቱትን የስነምግበር ጎደለቶች ለማረም የሚደረግ እንቅስቃሴ መኖሩ አጥጋቢ ባይሆን ተጠያቂነት ለማስፈን የሚደረግ ጥረት መጠናከር አለበት፡፡ ሰዎች ከሚተላለፉ ውሰኔዎችና ከሚወሰዱ እርምጃዎች የመማር እድል ሊፈጥር ስለሚችል ቀጣይነቱ ማረጋገጥ ከአመራሩ ይጠበቃል፡፡ የስነ ምግባር ደንብ በአግባቡ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማደረግ ላይ ክፍተቶች የሚታዩ መሆናቸው ግንዛቤ ውስጥ በመክተት አስፈላጊረ ስራ ተግባራዊ ማደረግም ከተቋመቱ የሚጠበቅ ነው፡፡

## 4.3. የተቋማት ግልፅነት

ተቋማት ራሳቸውን ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ዓላማቸውን ለማሳካትና አፈጻጸማቸውን ለማሳደግ ግልጽነት ሚናው የጎላ ነው፡፡ ግልፅነት ሙስናን ለመከላከል ከሚያስችል መሰረታዊ ተግባራት አንዱ ነው፡፡ ይህን ለማሳካትም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅና አሳታፊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቋማዊ ግልጽነት ማለት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥን ያጠቃለለ ነው፡፡ ግልፅነትን የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳ መልካም ውጤት ቢመዘገብም ሂደቱ የተአማኒነት እና የቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ከግምት በማስገባት በባህልና ስፖርት ዘርፍ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር የተገባ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም የዕቅድና በጀት ትግበራው የተሳካ እንዲሆን አጋዥ ሚናውን ተጫውቷል ተብሎ ይገመታል፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የዕቅድ ግምገማ የሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመለየት በሚያስችል መልኩ በጋራ ውይይት የተደረገባቸው መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከተቋማቱ አመራሮች ሰራተኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄዱ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና ብልሹ አሰራሮችን የመለየት ስራ መሰራታቸውን ከቀረቡ ሰነዶች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በግልባጭ እንዲደርሳቸው ከማድረግ ውጪ በብሮሸር፣ በዌብሳይታቸው፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ ተደራሽ ስለማድረጋቸው መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙት ተቋማት ውስጥ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የስራ ሂደቶቹ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚመለከታቸው አካላት የሚሳተፉ መሆናቸውን መረጃ ያቀረቡ ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስቱ ተቋማት መረጃ ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ከፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ በስተቀር ሁሉም የግዥና ጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በጋዜጣ እንደሚያሰራጩ ቢገልጹም ይህን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ካሉት ተቋማት ውስጥ ከብሄራዊ ቤተመዛግብት አገልግሎት በስተቀር የቀሩት ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው በቃል ቢገልጹም ስለማከናወናቸው መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ በማህበራዊ ሚድያ አጠቃቀም በኩል ያለው ልምድ በበጎ የሚታይ ሲሆን ሁሉም ተቋማት በሚባል ደረጃ ማህበራዊ ሚዲያ ኣካውንት ወይም ድህረገጽ እንዳላቸው ከምልከታው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አጥጋቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ አለመሆኑ፣ የበጀት አጠቃቀም መረጃ ለተገልጋይ የማሳወቅ ውስንነቶች፣ በተወሰኑ ተቋማት የሚመለከታቸው አካላትን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ለማሳተፍ አለመቻሉ በውሳኔዎች ተአማኒነት ላይ ጫና ሊያሳድር መቻሉ፣ውሳኔዎች እና ቃለ-ጉባኤዎች ተደራሽ አለመደረጋቸው አስተያየት የመሰብሰብ እድልን ያጠበዋል፣ ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ መሆን ላይ ያሉ ውስንነቶች መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ከዚህ በመነሳት ሊከሰቱ በሚችሉ የሙስና ስጋቶች

- በዚህ ዘመን መረጃ የሚጫወተውን ሚና ለሚገነዘብ ግልፅነት ሙስናን ለመዋጋት ምን ያክል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ በዘርፉ የአውቶሜሽን ስራ በተጠናከረ መንገድ ተግባረዊ አለመደረጉ መረጃ ማመንጨትና ማሰራጨት አዳጋች ሊደርገው እንደሚችል መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ስራ በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አለመደረጉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ግልፅነት ለማስፈን የሚደረገው ጥረት ከዘርፉ ባህርይ አኳያ ትዝበት ላይ የሚጥል ነው፡፡
- የሚወሰኑ ውሳኔዎችና እርመጃዎች በቃለ ጉባኤ ላይ መመስረት እንዳለባቸው እሙኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተቋመቱ የሚሰተዋለው ልምድ ቃለ ጉባኤዎችን ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማደረግ ላይ ክፍተት መኖሩን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን ሲሆን የሚወሰዱት እርመጃዎችን በትክክል የተወሰዱ ቢሆኑም ግልፅነት የጎዳላቸው ሊያስመስላቸው ይችላልና፡፡ የውሳኔ ቃለ-ጉባኤዎች ተደራሽ አለመደረጋቸው አስተያየት የመሰብሰብ እድልን ስለሚያጠበውም ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ስለሚከተው መቻሉ ጭምር ነው፡፡
- ዘርፉ ለመገናኛ ብዙሃን ካለው ቀረቤታ አንፃር ለጋዜጠኖች ተደራሽ በመሆን ላይ የሚሰራው ስራ የተጠናከረ ነው ብለን መውሰድ አይቻልም፡፡ ከተሰበሰበው መረጃ በሾሻል ሚዲያ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚበረታቱ ቢሆንም ግልፀነት ከማስፍን ያላቸው ፋይዳ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ እንቅስቃሴው የዜጎች ተሳትፎ ማሳደግ ካልቻለ እና አስፈላጊው መረጃ በመስጠት በኩል ክፍተት ካለበት ግልፅነት ያለው አሰራር ስለመኖሩ አስረጅ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ በተለይ ዘርፉ ከህብረተሰቡ ጋር ያለው መስተጋብር እና ቀረቤታ አንፃር የምርመራ ጋዜጠኝነት ማካሄድ ግልፅነት ለማስፈን የሚጫወተው ሚና ቢሆን የተሰጠው ትኩረት ግን አነስተኛ ነው፡፡

## 4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ያለባቸውን

ማሻሻል ተገቢ ነው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት በጥናቶች እና በዕለት-ተለት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመንተራስ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ እየተሰራ መሆኑ ቢገለጽም መረጃዎች ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ሁሉም ተቋማት ለሚገኙ አመራሮች እና ሰራተኞች ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ፀድቀው የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃም አልቀረበም፡፡

የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ በበብሄራዊ ቴያተር እና በብሔራዊ ቤተመዛግብት በህትመት እንደተዘጋጀ በምልከታ የታየ ሲሆን፤ ነገር ግን የተዘጋጀው የዜጎት ቻርተር ለተገልጋይ ተደራሽ ስለመደረጉም መረጃ አልቀረበም፡፡ በቀሪዎቹ ሶስት ተቋማት ላይ ግን የዜጎች ቻርተር ስለመዘጋጀቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች አኳያ የሚከተሉት ከአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጉዳዮች ተያያዥነት ሊኖራቸው የሚችሉ የዘርፉ የሙስና ስጋቶች፤

- አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ ከተወሰኑ ተቋማት ውጪ እየተሰራ ባለመሆኑ የቁጥጥር ሥርዓቱን ስለሚቀንስ ለሙስና ስጋት ሊያጋልጥ የሚችልበት እድል ሰፊ ነው፡፡ የሙስና ከሁኔታዎች ጋር ያለው የተለዋዋጭነት እና ዘርፉ ባህርይ ታሳቢ ያደረገ በጥናት ላይ የተመሰረተ አዳዲስ የማውጣትና የማሻሻል ስራ መስራት ካልተቻለ ሙሰናንና ብልሹ አሰራሮችን ጊዜው በሚመጥን አኳሃን ለመከላከል የሚደረግ እንቅስቃሴ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ አስተዋጾኦ ሊኖረው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተግባራዊ መደረጋቸው ብቻ በቂ ስለማይሆን ሙስናን ከመከላከል አንፃር ያመጡት ለውጥ ወይም የሚያሳድሩት ተፅኖ መመርመር እና ማጥናት ካልተቻለ ተጠያቂነት ለማስፈን ያላቸውን ጠቃሚነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከተዋል፡፡
- ለሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል እና ሌሎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሚኖራቸው ሚና የጎላ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህን ህጎች ላይ ግንዛቤ መፍጠሪያ መደረኮች ወይም ስለጠናዎችን በማዘጋጀት የአስፈፃሚውና ባለደርሻ አካለት የመስራት ልምድ አለመጎልበቱ ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ይህም በአፈፃፀም ላይ ክፍተት

ከመፍጠሩ ባሻገር ህጎች አለአግባብ ሲጣሱ ለማረም የሚኖረው እድል ጠባብ ሊያደርገው እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም፡፡

- የዜጎች ቻርተር ያዘጋጁ ቢኖሩም ለተጠቃሚ ተዳረሽ በማድረግ በኩል የተሰራው ስራ ግን አጥጋቢ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ስለሆነም ዜጎች አገልግሎት በሚገኙበት ጊዜ ግዴታቸውና መብታቸውን ስለማያውቁ ለአላስፈላጊ እንግልትና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## 4.5. የንብረት አስተዳደር

የአንድ ንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ ይህ የተገዙ ንብረቶች መረከብን፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅን፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በሁሉም ተቋማት የቢን ካርድ እና የቋሚ ንብረት ምዝገባ አጠቃቀም ስርዓት ያለ ሲሆን የተሟላ የአውቶሜሽን ስራ IFMIS የተተገበረበት ሁኔታም አለ፡፡ በሌላ በኩል ከንብረት አያያዝ ጋር የሚጠቀሰው ጉዳይ የካይዘን ንብረት አሰተዳደር ስርዓት ሲሆን ስርዓቱ በሁሉም ተቋማት ተግባራዊ ስለመደረጉ የቀረበ መረጃ የለም፡፡ በዘርፉ ከሚገኙት ተቋማት ውስጥ አራቱ አመታዊ የንብረት ቆጠራ እንዳካሄዱ ከሪፖርቶች ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፤ የብሄራዊ ፀረ-አበረታች ኤጀንሲ አመታዊ የንብረት ቆጠራ ስለመካሄዱ የቀረበ መረጃ የለም፡፡ ወቅታዊ የንብረት ቆጠራ አለማድረግ በንብረት አስተዳደር ላይ የሚደረግ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በማላላት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

በ2014 ብሄራዊ ቤተመዛግብት ብር 186,969 የሚያወጡ የተለያዩ ቆርቆሮዎችን በሽያጭ ያስወገደ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ብር 203,760 የሚያወጡ ብዛታቸው 33 የሆኑ የተለያዩ ስፖርት ዕቃዎችን በስጦታ ያስተላለፋቸው ንብረቶች መሆናቸውን ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የቀሩት ሶስት ተቋማት ምንም አይነት የንብረት ማስወገድ ስለማካሄዳቸው መረጃዎች

አልቀረቡም፡፡ በስፖርት አካዳሚ፤ በፀረ-አበረታች እና ብሄራዊ ቤተመዛግብት የሚወገዱ ንብረቶች ተገቢው ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገላቸው ሲሆን፤ በቀሩት ሁለት ተቋማት ግን ጥበቃና አያያዝ ስርዓቱ በቂ እንዳልሆነ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ንብረቶች ለጉዳት ወይም ለስርቆት የተጋለጡ እንዲሆኑ በማድረግ የመንግስት ሀብት ሊባክን የሚችልበትን ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

ከዚህ በመነሳት ሊከሰቱ በሚችሉ የሙስና ስጋቶች

- በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት በንብረት አስተዳደርና ቋሚ ንብረት ምዝገባ እየተደረገ መሆኑ በበጎ ጎን የሚታይ ነው፡፡ ሆኖም ዓመታዊ ቆጠራ ስለ መካሄዱ መረጃዎች ቢኖሩም በቆጠራ ሪፖርት መሰረት ስለተወሰዱ የማሻሻያ ስራዎች የሚያመላክት መረጃ ግን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህም በተቋማት ያለው የንብረት አስተዳደር ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ስለዚህ ተቋማት የንብረት ቆጠራና አስተዳደር ስርአት ተጠያቂነት በሚያጎለብት መልኩ ተግባራዊ መደረጉን የማረጋገጥ ስራ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በተወሰኑ ተቋማት የሚታየወን ለንብረት የሚደረገው ተገቢው ጥበቃና ቁጥጥር ክፍተት የሚታይበት ሁኔታ መኖሩ የመንግስት ንብረቶችን ለስርቆትና ብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ :
- በተጨማሪም በየተቋማቱ የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ በአውቶሜሽን እና በካይዘን አሰራር የታገዘ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የንብረት አስተዳደር ዘመናዊ አሰራር የተከተለ እንዳይሆን አድርጎታል ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡ በአውቶሜሽን የታገዘ የካይዘን ስርኣት ተግባራዊ አለመደረጉ የንብረት አስተዳደሩ ዘመናዊነት ያለተከተለ ስለሚሆን ለብክነት የተጋለጠ ሊያድረገው እንደሚችል ማሳያ ነው፡፡ የተጠናከረ በአውቶሜሽን የታገዘ የንብረት አያያዝ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመኑ ተደጋጋሚና አላስፈላጊ ግዥዎች ለማካሄድ የሚያስችል እድል ሊያሰፋው ስለመቻል ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ መሆኑን ተቋማት መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተቋማቱ ንብረት የማስወገድ ስራ መስራታቸው የሚመላከቱ መረጃዎች ቢገኙም የማስወገድ ስራ በባለ ሙያዎች ጥናት ስለመመስረቱ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ የተቋቋመ አስወጋጅ ኮሚቴ ስለመዋቀሩም የሚያሳየይ ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የጥናት መረጃው ተደራሽ አለመሆኑ የማስውገድ ስራው በባለ ሙያ ሳይሆን በማንጅመንት ውሳኔ ላይ የተመሰረተ ሊያደርገው ስለሚችል ተገቢው አሰራር መከተሉን ማረጋገጥ ከአመራሩ የሚጠበቅ ነው፡፡

## 4.6. የግዥ አስተዳደር

ድርጅቶች ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለማሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኖታል፡፡ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ የብሄራዊ ፀረ-አበረታች እና ባህልና ስፖርት ሚ/ር የስራ ክፍሎችን የግዥ ፍላጎት መሰረት በማድረግ የግዥ እቅድ ያዘጋጁ ሲሆን፤ የቀሩት ሦስቱ ተቋማት ግን የግዥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ዕቅድ ለማዘጋጀታቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ በሁሉም ተቋማት የግዥ አፈጻጸም ግምገማ ስለመካሄዱ የሚያሳዩ መረጃዎች አልቀረቡም፡፡

በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት መካከል ብሄራዊ ቴያትር እና ስፖርት አካዳሚ ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ግዥ የሚፈፀም መሆኑ ቢገለፅም ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ ግን አልተገኘም፡፡ ቀሪዎቹ ሶስት ተቋማት ግን ስቶክን መሰረት ያደረገ ግዥ እንደሚፈፀም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግዥዎች በፊት የገበያ ዋጋ ጥናት እንደሚከናወን የሚያሳዩ መረጃዎች አልቀረቡም፡፡

በዘርፉ ከተከናወኑ ግዥዎችን ውስጥ፡-

- በብሄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመፃህፍት የገንዘብ መጠናቸው ከ2.7 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆኑ በዋጋ ማቅረቢያ፣ ከ2.6 ሚሊዮን ብር በላይ በውስን ጨረታ፣ 555,386 ብር በቀጥታ የግዥ ዘዴ ከአንድ አቅራቢ የተከናወኑ ግዥዎች መኖራቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የብር መጠኑ 262 ሺህ የሚሆን የግዥ ሂደት ላይ ደግሞ የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦበት እንደተሰረዘ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡
- ባህልና ስፖርት ሚ/ር ከ7.2 ሚሊዮን ብር በላይ ከዕቅድ ውጭ፣ ቁጥራቸው 21 የሚደርሱ የገንዘብ መጠናቸው 9.3 ሚሊዮን ብር የሚሆን በፕሮፎርማ፣ 300 ሚሊዮን ብር በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ግዥ የተፈፀመ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ፀረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ግዥ የተከናወነ መሆኑን ከዋና ኦዲተር የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

- ብሔራዊ ቴያትር 5.7 ሚሊዮን ብር በላይ በፕሮፎርማ ግዥ ዘዴን በመጠቀም ግዥ የተፈፀመ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥን (EGP Electronic Government Procurement) በተመረጡ ድርጅቶች እንዲተገበሩ በያዘው አቅጣጫ መሰረት በዘርፉ ስር ባሉ ሁሉም ተቋማት የአተገባበር ስራው በጅምር ላይ እንዳለ ተገልጿል፡፡ ተቋማት የEGP ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚያበረታታ ነው፡፡ ይህ የግዥ ስርአት ሀብትን በቁጠባ ለመጠቀምና በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ሲሆን በጅምር ላይ ያሉ ተቋማት የማዘመኑን ስራ በማጠናቀቅ ቀድሞ ከነበሩበት የማንዋል ሥራ ወደ ዲጂታል ሲስተም በፍጥነት እንዲዛወሩ ግፊት ያስፈልጋል፡፡ በ2014 የበጀት ዓመት ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በዘርፉ ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት ቅሬታ ቀርቦ እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች አለመኖራቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ በጎ ልምድ ሊበረታታና ሊቀጥል ይገባዋል፡፡

የተቋማት ግዥ ስርአትና አፈፃፀም በተመለከተ ሊጠቀሱ ከሚችሉ የሙስና ስጋቶች የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- አብዛኛው የተቋማት ግዢዎች የሚፈፀሙት በፕሮፎርማ የሚገዙ ከፍተኛዉን ድርሻ የሚይዙ ናቸው፡፡ ይህ አሰራር ግዥዎች በቁጥቁጥ መንገድ የሚፈፀሙ በመሆናቸው አኳያ አብዝቶ በመግዛት የሚገኘውን የዋጋ ቅናሽ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡ የፕሮፎርማ ወይም ቁጥቁጥ ግዢ የጨረታ ሰነድ መሰብሰብ ስራ በአብዛኛው በቀጥታ በግዢ ሰራተኞች የሚካሄደው በመሆኑ ለጥቅም ግጭት ተጋላጭ የመሆኑ ስፊ ነው፡፡ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ሆን ብሎ ግዥዎችን በመከፋፈል በቁጥቁጥ መፈፀም በመመሪያ የተከለከለ ተደርጓል፡፡ በዘርፉ ያሉ ተቋማትም የገበያ ጥናት የማካሄድ ልምድ የሉላቸው መሆኑን በመረጃ ስበሰባው ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለይ ግዢው በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን የተጋነነ ዋጋ የመቅረብ እድሉም ያሰፋዋል፡፡ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ማደረግ ካልተቻልም የግዢ ሰራተኛውም ሂደቱን ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማመቻቸት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ጥቅም ላይ ሊያውለው ስለሚችል አሰራሩ ለእምነት ማጉደል ሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ ግዥ የሚፈፀምበት ሁኔታ መኖሩን

መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ ይህ ግዥ በተጠናና ህጋዊ አሰራር በተከተለ መልኩ ማይፈፀም ከሆነ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርገው እንደሚችልም መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

- ኤሌክትሮኒክ ግዥ ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ በመፍጠር የግዥ ሂደቶችን ቀላል እና ለአቅራቢዎች ወይም ለንግድ ማህበረሰብ እኩል እድሎችን በመስጠት የመንግስት ግዢን ግልፅነት የተላበሰ በማድረግ ብልሹ አሰራሮችን ለመቀነስ አስተዋፅኦው የጎላ ነው፡፡ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ማዘመኑ በጨረታዎች ላይ የተወዳዳሪዎች ቁጥር ከመጨመር ባሻገር በሂደቱ ላይ ግልፅነት ለማስፈን እንደሚያግዝ ታሳቢ ማደረግ ተገቢ ነው፡፡ ሃላፊነታቸውን በማይወጡ አቅራቢዎች ላይ መረጃ በማመንጨት ሙሰናን ለመዋጋት አጋዥ ሚናም ይጫወታል፡፡ የሰው ለሰው ንክኪ ስለሚቀንሰውም የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ለማድረግም አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- ግዥ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው በስቶክ ስለመኖሩ በንብረት ክፍል ማረጋገጫ አለመስጠት አላግባብ ግዥዎችን በመፈፀም የንብረት ክምችትን የሚፈጥር ከመሆኑም በተጨማሪ ግዥዎችን በዕቅድ አለመፈፀም ግዥዎች አስገዳጅ ናቸው በሚል የተቀመጡ አሰራሮችን ባልተከተለ መልኩ እንዲፈፀሙ ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለሆነም የንብረት አስተዳደር ስርአቱ የማዘመን ስራ አላግባብ የሚፈፀሙ ግዥዎች ለማስቀረት በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ ማደረግ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡

## 4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያለው የሰው ሀብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ኃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ የብሄራዊ ቤተመዛግብት እና የብሄራዊ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ አዲስ ቅጥር ለመፈጸም በጋዜጣ ማስታወቂያ ማውጣታቸውን ካቀረቡት መረጃ ለመረዳት ተችሏል፤ የቀሩት ሶስቱ ከ2014 ጀምሮ ቅጥር የቆመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በሁሉም

ተቋማት የሰራተኞች ቅጥር፣ ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ ቅሬታን በተመለከተ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ከጂኤጂ ምደባ ጋር ተያይዞ በአንድ ተቋም ብቻ አመስት ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን፤ አምስቱም በወቅቱ መፈታታቸው ተገልጿል፡፡ በተቀሩት ተቋማት ቅሬታ አልቀረበም፡፡ የአመራር ምደባን በተመለከተ በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በውድድር የሚመድቡ መሆናቸውን በሰነዶች ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እና የስራ ልምድ ማጣራትን በተመለከተ ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ስለመስራታቸው መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ የሰው ሀብት መረጃን በተመለከተ በተቋማቱ ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት የማደራጀት ጅምር ስራዎች እንዳሉ ከወጡ ማስታወቂያዎች፣ በቃለ-ጉባኤ ምልከታ እና ከተተገበሩ ሲስተሞች ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለአብነት ባህልና ስፖርት እንዲሁም ብሄራዊ ቤተመዛግብት የተቀናጀ የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ሥርዓት (Integrated Civil Service Management Information system (ICSMIS)) በማበልፀግ ስራ ላይ አውሏል፡፡

የተሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ፡-

- በብሄራዊ ፀረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ አንድ የሙያ ብቃት ማጎልበቻ ስልጠና ለ59 አመራርና ሰራተኞች የተሰጠ መሆኑ፣
- በባህልና ስፖርት ሚ/ር በአመራር ዘይቤ፣ የለውጥ አስተዳደርና ፖሊስና ስትራቴጂ ላይ ለ63 አመራርና ሰራተኞች የተሰጠ መሆኑ እና
- ብሄራዊ ቤተመዛግብት 4 የሙያ ብቃት ማጎልበቻ ለ203 አመራርና ሰራተኞች፣ 1 የስነምግባር ማሻሻያ ለ159 አመራርና ሰራተኞች የተሰጠ መሆኑ ከተሰበሰበ መረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ ሁለት ተቋማት ስልጠና ስለመስጠታቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

አብዛኛው ተቋማት ትኩረታቸው የአቅም ግንባታ ላይ ሲሆን፤ ለስነምግባር ስልጠና የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡

ከሰው ሀብት አስተዳደር ጋር ተያያዘው ሊነሱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች

- የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃዎች ማጣራቱ ስራ መተግበሩን የሚያሰዩ መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡ ሃሰተኛ ሰነዶች በመጠቀም የሚቀጠሩ ሰራተኞች በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት ባሻገር ሰራተኛው የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነድ በማስመሰል የማዘጋጀት ሙስና መፈፀሙ አመላካች ነው፡፡ በተጨማሪም ዜጎች ማግኘት ያለባቸውን የስራ እድል በመዝጋት ተገቢው ልምድና እውቀት ዋጋ እንዲያጣ ስለሚያደርገው በመንግስታዊ ቅጥር ላይ አሉታዊ ምስል ሊፈጥር መቻሉን ግምት ውስጥ በመስጠት ትልቅ ትኩረት መሰጠት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል፡፡
- ከተገኘው መረጃ መረዳት የሚቻለው ተቋማት የሰራተኛው አቅም ለማጎልበት ስልጠና እየሰጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ዘርፉ ለአገር ካለዉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ከሚያሳትፈው የሰው ቁጥር አኳያ ስነምግባር ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን አለመሰጠታቸው የአቅም ግንባታ ስራው የተሟላ እንዳይሆን ሊያደርገው እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ በተለይ በስነምግባር ዙርያ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን የዘርፉ አመራር መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ ለስልጠና የሚያስፈልግም ሀብት መመደብም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- የሰው ሃበት አስተዳደሩ ስርአቱ በአውቶሜሽን የማዘመን ስራ በውስን ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራዎች እንዳሉ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ትግበራው አጥጋቢ ደረጀ ላይ አለመሆኑን ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ያደርገዋል፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት አስተዳደር ተግባራዊ አለመሆኑ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅም ተገቢ ነው፡፡

## 4.8. የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ

የአገሪቱ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ህግ በሚደነግገው መሰረት የፌዴራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ሀብታቸውን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተቋማትም ቅጥር ከመፈፀማቸው በፊት የመጀመሪያ ወይም ዳግም ምዝገባ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ብሔራዊ ፀረ አበረታች እና ብሔራዊ ቲያትር ሀብት ምዝገባ ስራ ለመጀመራቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ የቀሩት ሦስቱ ተቋማት የአመራር እና የሰራተኛ ሀብት ምዝገባ መረጃ እንሚያሳየው ማስመዝገብ ካለባቸው ባህልና ስፖርት ሚ/ር 5 አመራሮች ማስመዝገባቸውን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፤ እንዲሁም ከ330 ሠራተኞች መካከል ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ ያስመዘገቡት 39 ብቻ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ማስመዝገብ ከሚገባቸው 4 አመራሮች አራቱም አስመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም ከ178 ሠራተኞች መካከል 150 አስመዝግበዋል፡፡ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት ማስመዝገብ ከሚጠበቅባቸው 12 አመራሮች 2 ብቻ አስመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም ከ318 ሠራተኞች መካከል 45 ብቻ እንዳስመዘገቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአጠቃላይ በዘርፉ ማስመዝገብ የሚጠበቅባቸው አመራሮች 21 ሲሆኑ ያስመዘገቡት 6 (28%) ብቻ ናቸው፡፡ ሰራተኞችን በተመለከተ 826 ሲሆኑ ሀብት ያስመዘገቡት 234 (28%) ሰራተኞች ናቸው፡፡ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓት የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ምንጫቸው ያልታወቀ (ተገቢ ያልሆኑ) ንብረቶችን ለመለየት ካለው ፋይዳ አንፃር በዘርፉ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ አለመደረጉ እንደስጋት ምንጭ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- የሀብትና ንብረት የመመዝገብ እየተካሄደ ቢሆንም መረጃዎቹ የሚያሳዩት ግን አፈፃፀሙ በአጥጋቢ ሁኔታ እየተካሔደ አለመሆኑን ነው፡፡ አብዛኛው በኦን ላየን የተመዘገቡ አለመሆናቸው ሲታይ ደግሞ አፈፃፀሙ ምን ያክል የመመዝገቡ ስራ በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ ያሳያል፡፡ የኢንተርኔት አገልግሎት መቆራረጥ በኦን ላየን የመመዝገብ ሂደት ላይ እክል መፍጠሩ ተጠቅሷል፡፡ መመዝገቡ ተጠያቂነት ማስፈን ካልቻለ ግቡን መቷል ብሎ መውሰድ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## 4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

በባህልና ስፖርት ዘርፍ ስር የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት ምንም አይነት ፕሮጀክት ስለሌላቸው በፕሮጀክት አስተዳደር መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የገንዘብ መጠኑ ከ3.3 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን የግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቀና ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆኑ፤ የገንዘብ መጠኑ 16.4 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን የግንባታ ፕሮጀክት የኮንትራት ውል ስምምነት የተቋረጠ መሆኑ፤ የገንብ መጠኑ 21.2 ሚሊዮን በላይ ተቋራጩ የተከሰሰበት ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በብሔራዊ ቤተመዛግብት የገንዘብ መጠኑ 450 ሚሊየን ብር በጊዜው ያላለቀና የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ፣ በተደጋጋሚ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው፣ ተጨማሪ ስራ የተሰጠባቸው እና ግዙፍ በጀት ስለሚፈስባቸው የሙስና ስጋት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤**

- በዘርፉ እየተተገበሩ ያሉት ፐሮጅቶች በሚፈለገው መንገድ እየተጠናቀቁ አለመሆናቸውና ተጨማሪ ወጪ እየጠየቁ መሆናቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለፐሮጅክቶች የዋጋ ማስተካከያ ተደርጎ የማስቀጠል ስራ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ያለው የፐሮጅክቶች አስተዳደር ስርኣቱ በአግባቡ ካልተማራም ለሙሰና ተጋላጭ ሊያደርጋቸው መቻሉ ይታመናል፡፡ መፀደቅ የማይገባቸው ጨረታዎች በማፅደቅ ወይም ማሸነፍ የማይጋባቸው ተጫራቾች እንዲያሸንፉ በማደረግ የሚከሰት ብልሹ አሰራር ሊከሰት ይችላል፡፡ ውጤቱም የመንግሰት ፐሮጅቶች በተመደበላቸው በጀት እና ጊዜ እንዳይጠናቀቁ በማድረግ የህዝብ ሀብት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚፈጠሩ ችግሮች ከሙስናና ብልሹ አሰራር የሚመነጩ ናቸው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ በመሆኑ በፐሮጀክት አስተዳደር ዙርያ የሚታዩ ችግሮች ለመፍታት ጥልቅ የሙስና ስጋት ጥናት ተገቢ ያደርገዋል፡፡ ይህም በፐሮጀክት አስተዳደር ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች በመረጃና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ለመፍታት የሚኖረውን እድል ያሰፋዋል፡፡

## 4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የውጭ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች የኦዲት አስተዳደር ስርአት በጥናቱ የታየ ሲሆን በባህልና ስፖርት ዘርፍ ዉስጥ ባሉ ድርጅቶች ያለው አሰራር እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡ በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሁሉም ተቋማት በየአመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ከሪፖርቶች መገንዘብ ተችሏል፡፡ የኦዲት ስራ በተከናወነባቸው ተቋማት በኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የሚካሄድ መሆኑን ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በኦዲት ሪፖርት ግኝት መሰረት የተደረጉ ማሻሻያዎችን በተመለከተ የኦዲት ስራ በተከናወነባቸው ሁሉም ተቋማት ማሻሻያዎች እንደተደረጉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ተቋማት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን

ለሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር አለመኖሩን ከተጻፉ ደብዳቤዎች ለማየት ተችሏል፡፡

የ2013 እና 2014 በጀት ዓመት የተቋማት የኦዲት ግኝቶች መሰረት በተደጋጋሚ ከተነሱ ችግሮች የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

- በብሄራዊ ቤተመዛግብት 1.2 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ፣
- በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ከ2.2 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተሰበሰበ እና ከ1.5 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተከፈለ ሂሳብ መኖሩ
- በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ከብር 54500 ከዕቅድ ውጪ በፕሮፎርማ ግዥ መፈፀሙ የሙስና ስጋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡
- በብሄራዊ ትያትር ቤት 1.4 ሚሊዬን ብር ለማን እንደሚከፈል እና እንደተከፈለ የማይታወቅ ገንዘብ በኦዲት ግኝት መኖር፤በፍርድቤት ውሳኔ የቀድሞ ቴያትር ቤት ዳይሬክቴሩ 196896.50 ብር እንዲከፍሉ የተወሰነ ቢሆንም እስካሁን ድረስ እንዳልተሰበሰበ ግኝቱ ያሳያል፡ :

ከዚህ በመነሳት የሚከተሉት ስጋቶች መለየት ይቻላል፡፡

- የኦዲትና ቁጥጥር ስርዓት የመንግስትን ሀብት ከብክነት ለመታደግ፤ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመከላከል ያለው ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዋናነት አመራሩ በኦዲት ግኝት ተመስርቶ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም በኦዲት ግኝት ላይ ተመስርተው የተወሰዱ እርምጃዎች የሚሳይ መረጃ በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት ማግኘት አልተቻለም፡፡ የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ መሆናቸው የሚያሳይ መረጃም አልቀረበም፡፡ ሪፖርቶች ተደራሽ አለመሆናቸው አመራሩ አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት ያለው ተነሳሽነት ውስን መሆኑን አመላካች ነው፡፡
- የኦዲት ሪፖርት በተመለከተም ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት በተለይም ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ ለህግ ፣ለተቋማዊ ለዉጥና የመገናኛ ብዙሃን በተደራጀ መልኩ ተደራሽ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ይህም የሙስና ስጋቶች በጋራ በመየት የተቀናጀ ስልትና ፖሊሲ በመንደፍ በተቋም ደረጃ ሙስናን የመከላከል ስራ ለመከወን አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አንጻር ከላይ የተጠቀሱት

ክፍሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ከዘርፉ ተቋማት አመራሮች ይጠበቃል፡፡

## 4.11. የተቋማት የሙስና ስጋት ትንተና

በባህልና ስፖርት ዘርፍ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ለሙስና ስጋት ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

- **ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳላቸው የተገለጹ አሠራሮች፡** የግዥ ስርአት፣ ንብረት አስተዳደር እና ከቤተመዛግብት ጋር ተያይዞ መረጃ ሀብቶች አስተዳደር
- **መካከለኛ የሙስና ተጋላጭነት እንዳላቸው የተገለጹ አሠራሮች፡** ሰው ሀብት አስተዳደር፣ የመረጃ ሀብቶች አሰባሰብ ስራ፣ የስፖርተኞች የፀረ-አበረታች ምርመራ፣ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጋር በተያያዘ የኢንተለጀንስ አሰራር እና የህግ ጥሰቶች የዳኝነት ሂደት የተጋላጭነት ደረጃቸው መካከለኛ ደረጃ እንደሆነ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# ክፍል አምስት

# መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ

## 5.1. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የነበረው፣ የባህልና ስፖርት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመዳሰስ የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አቢይ ዓላማ ስር በጥናቱ መቋጫ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡ አምስት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፡- 1ኛ. የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣ 2ኛ. የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ እና 3ኛ. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በሪፖርቱ ላይ ከቀረቡትን አበይት የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግየሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

1. በተቋመት ውስጥ ያሉት የስነምገባር ክፍሎች በሰው ሃይል እና በተለያዩ ግብአቶች የተሟሉ አለመሆናቸው ይታያል፡፡ ስነምግባር ክፍሎችም የበጀት ነፃነት ያላቸው አይመስልም፡፡ ይህ አቅዶ ስራው እንዳይሰራ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተደራጀ መልኩ ለመዋጋት የሚያስችል ቅንጅታዊ ስራ እየተሰራ አመሆኑን ታይቷል፡፡

2. በጥናት ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ተጠያቂነት ስራ እየተሰራ አለመሆኑን በሙስና ስጋት ዙርያ እና በተገልጋዮች እርካታ ላይ ጥልቀት ያላቸው አለመካሄዳቸው እንደማሳያ ሊቅርቡ ይችላሉ፡፡
3. የመረጃ ተደራሽነት ሰራዎችም እስከ ሰራተኛው ድረስ ማረጋገጥ የሚያስችሉ ግልፅነትን ማስፈን የሚያስችሉ ስራዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው መመልከት አልተቻለም፡፡ በአብዛኛው የእቅድና አፈፃፀም መረጃዎችና ሪፖረቶች በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ አከባቢ ላይ ተንጠልጥሎ የመቅረት ልምድ እንዳለ ለማስታዋል ተችሏል፡፡
4. በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ዙርያ ለአስፈፃሚው አካል ስለጠና የመስጠት ልምድ አለመዳበሩ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም ተገቢው ጥናት በማካሄድ ህጎችን የማሻሻልና አዳዲስ የማውጣት ስራ አለመታየቱ እንደ ክፍተት መውሰዱ ተገቢ ነው፡፡ አስፈላጊው የስነምግባር ደንብ አውጥቶ ተግባራዊ ማደረግ ላይ ውስንነት ይታያል፡፡
5. የንብረት አስተዳደር ለማዘመን የሚያስችሉ የካይዘን እና የአውተሜሽን ስርኣት በተፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተስተውሏል፡፡
6. አብዛኛው የተቋማት ግዝዎች በቁጥቁጥ መንገድ የሚፈፀሙ መሆናቸውን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ተስተውሏል፡፡
7. በዘርፉ ባሉ ተቋማት የአስፈፃሚው ስነምግባር ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ስለጠናዎች አየተሰጠ ቢሆን ስነምግባር ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች አለመኖራቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡
8. ሃብት የማሳወቅና መመዝገብ ያለበት አፈፃፀም ደረጃ ከፍተኛ ውስንነት የሚታይበት ነው፡፡ ስራ አጥጋቢ ሊባል በሚል ደረጃ ተግባራዊ አለመሆኑን ትኩረት የቤት ስራ መሆኑን አመራሩ መገንዘብ አለበት፡፡
9. የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ አለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮች እና ሙሰናን ለመዋጋት የሚስችል ሁኔታ አለመፈጠሩ ነው፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

- አሁን ያለውን አደረጃጃት በመፈተሽ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ነፃነቱን ጠብቆ (ከአመራሩ ጣልቃ ገብነት) ከሌሎች ክፍሎች በቅንጅት ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት በሚስችል ደረጃ የማደራጅት ስራ ቢሰራ፡፡ በተጨማሪም የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ያቀዳቸዉን ተግባራት በተገቢዉ መንገድ እንዲያከናዉን ለክፍሉ ቁርጥ በጀት (በራሱ አርዕስት) ሊኖረዉ ይገባል፡፡
- ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አንጻር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የዉስጥ ኦዲት፣ የህግና ተቋማዊ ለዉጥ የስራ ክፍሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ይገባል፡፡
- በተጠናከረ መልኩ ጥልቅ የሙስና ስጋት እና የደንበኞች እርካታን ጥናቶችን በማካሄድ ብልሹ ተግባራትና ሙስናን በመለየት ተጠያቂነት ማሰፈን የሚያስቸሉ ስራዎች ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የተቋማት የጥቆማ ስርአቱን ዘመናዊና ሚሰጢራዊነቱ የጠበቀ እንዲሆን መስሰራት አለበት፡፡
- የመረጃ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዘመናዊና የተደራጅ አሰራር በመዘርጋት ለባለድርሻ አካላት በፍጥነትና በጥራት መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፡፡ የዕቅድ እና አፈፃፀም ግምገማዎች የተቋማቱ ሰራተኞች በሚያሳትፍ መልኩ ተግባራዊ ማደረግ፡፡
- በጥናት ላይ ተመስርቶ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ከማሻሻልና ማውጣት በተጨማሪ ለአመራሮች እና ሰራተኞች ስልጠና መስጠት፡፡ ተግባራዊ የሚደረጉ ህጎች የሚያመጡት ተፅኖ ላይ ጥናት ማካሔድ እና አሰፈላጊው ክትትል ማድረግ፡፡
- የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ ዘመናዊት እንዲላበስ በአውቶሜሽን የታገዘ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ ማድርግ፤ በተሟላ መልኩ የንብረት ቆጠራ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማከናወን፣
- የግዥ ሥርዓቱን ለማሻሻል የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላና በተደራጀ መልኩ ተግባራዊ ይኖርበታል፡፡ ግዢ ከመከናወኑ በፊት የገበያ የዋጋ ጥናት በማከናወን በተጋነነ ዋጋ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን ማስቀረት የሚያስችል አሰራር ቢዘረጋ፣

- የሰዉ ሃብት ብቃት እና ስነምግባር ግንዛቤ ማሳደግ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ማካሄድና ለስራው የሚያስፈልግም በጀት መመደብም፡፡ የትምህርትና ስራ ልምድ ሰነዶችን የማጣራቱ ስራም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ውስጥ ያሉ ፕሮጅክቶች የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው እንደሆኑ በጥናቱ ለማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነኚህ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ በጀት የሚያንቀሳቅሱ በመሆናቸው በቀጣይ በፕሮጀክት አስተዳደር ዙሪያ ጥልቅ የሆነ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል የሚያስችል ጥናት ማካሄድ ቢቻል፣
- በዘርፉ የሚገኙ አመራርና ሰራተኞች ሀብት ምዝገባ በተጠናከረ መልኩ ማስቀጠል፡፡
- የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖረቶች ተደራሽ በማደረግ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል ስራ በመስራት የመንግስትን ሀብት ከብክነት መታደግ፤ በሪፖረቶች ላይ ተመስርተው የሚወሰዱ እርመጃዎችም ግልፅነት በተመላበት መንገድ ማሳወቅ፡፡

## Reference

1. Hwang, Geumchan (2016, April) Understanding Sport Corruption: An Examination of People's Perceptions Toward Corruptions, Psychology Research, Vol. 6, No. 4, 250-257 doi:10.17265/2159-5542/2016.04.005
2. United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC) (2021) Global Report on Corruption in Sport, United Nations
3. Siegel, Danielle (2016) Lights, Cameras, and FCPA Actions: The Problem of Foreign Corrupt Practices by Hollywood, NYSBA Entertainment, Arts and Sports Law Journal, Vol. 27, No. 3
4. Dalena, Anna Lucky (2016) Protecting Cultural Heritage in Times of Instability Tunisia, a case study, Master's Thesis, Faculty of Juridical, Political and Social Sciences of Tunis, University of Carthage